ፓኖራማ  ቁጥር 60

የትዝብት አድማስ

የካቲት 8 ቀን 2001

# <u>ጦርነት የፈጠራቸውን ሌቦች፥ ሠላም ትሰቅላቸዋለች</u>

ርዕሱን የጠቀስነው ጆርጅ  ሀርበርት  ከተሰኘ  አንድ  የመረጃ ጠበብት ንግግር ነው፡፡ ለጦርነቶች  መንስዔ  የሚሆኑ  የተለያዩ  ምክንያቶች  እንደነበሩና ወደፊትም እንደሚኖሩ ግልፅ ነው፡፡ “ በማር ጠብታ ሀገር ተፈታ” በተሰኘው ግጥማቸው፥ ደራሲ  ከበደ  ሚካኤል  በጣም  ትንሽ  ነገር  በቆሰቆሰችው አለመግባባት፥ የአንድ ሀገር ነዋሪዎችን  ከሚያፋጅ ጦርነት ጀምሮ ፥ እስከ ብሄራዊ ዓላማና ግብ  ከአነገበ  ጦርነት ድረስ   በዘመናት በርካታ  ጦርነቶች መካሄዳቸውን የዓለም ታሪክ  እንደመዘገበው ያስረዳሉ፡፡ ለዝርፊያ፥ ለበቀል፥ ለመከላከል፥ መብትንና ሰበዓዊ  ክብርን  ለማስጠበቅ ፥ ከጥቃት ለመዳን ፥ የሀገርን  ነፃነት ለማግኘት ሀበት ንብረትን ቤተሰብንና ወገንንም ከግፈኞች ለመጠበቅ፥ ወዘተ. በዓለም ውስጥ ቁጥራቸውን ለመወሰን ያልተቻሉ ጦርነቶች ተደርገዋል፡፡ አምባገነኖችና ቅኝ ገዢዎች ለጥቅማቸው ሲሉ ብዙ ደም ያፈሰሰ ጦርነት ፈጥረዋል፡፡ በመደብና በሃይማኖት በዘርና በመሬት ምክንያት በተደረጉ ጦርነቶች፥ደቂቀ-አዳምና ሔዋን እንደ ዝንብ  ረግፈዋል ፡፡ በሁሉም  ጦርነቶች ሌቦች ተፈጥረዋል፡፡  ሠላም  ሲሰፍን  ደግሞ  እነኝህ ሌቦች  በፍርድ፥  እንደ ወንጀላቸውና ተግባራቸው  ተቀጥተዋል፡፡ተሰቅለዋል፡፡ ዕልፍ አዕላ  የሆኑትን  የኢትዮጵያን ዜጎች ያስጨፈጨፈው ቬኒቶ ሙሶሊኒ  ሰላም ሲሰፍንበገዛ ሀገሩ በኢጣሊያን ሕዝብ ተዘቅዝቆ ተሰቅሏል፡፡  በጦርነት  የተፈጠሩት ሌቦች ሁሉ በሠላም ጊዜ  እንደሚሰቀሉ የሙሶሊኒ  የመጨረሻው  ዕጣ  ፈንታ  ታሪካዊ ምስክርነቱ ህያው ሆኖ ይኖራል፡፡

ዛሬ በሀገራችን በብሄረሰብ የተደራጁ ጥቂት ሰዎች የሌብነት ተግባራቸውን ለማሳካት ሲሉ የማፍያ ማለትም የዘራፊ ወንበዴ ድርጅት አቋቁመው ኢትዮጵያን በሁለንተናዊ ገፅተዋ እየዘረፏት ይገኛሉ። ሌብነቱና ዝርፊያው፥ እንኳን ተዘራፊውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ቀርቶ ፥ እነርሱ እራሳቸውን ዘራፊዎቹን ጭምር ሳይቀር ሊያምኑት በማይችሉት ደረጃ እያስገረማቸው ይገኛል።የወያኔ ወንበዴና ዘራፊ ቡድን አባሎች ለአለፉት18 ዓመታት ወዲህ ብቻ የዘረፉትን መጠን አልባ ሀብትና ንብረት ከግምት በላይ ነው ብሎ ከማለፍ በስተቀር፥ በዕርግጠኝነት ልኩን በምናልባታዊ አባባል ለመናገር እንኳን ቢሆን የሚቻል አልሆነም።ይህን ለማድረግ ፥ በሙያው የተካኑት ጠበብቶችና መርማሪዎች የወደፊት የተግባር ድርሻ ይሆናል።ታዲያ ብሄራዊ ሀብት ንብረት ከመዝረፋቸው ባሻገር ፥መተኪያ የማይገኝለትን፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ፥ ሰብዕና ታሪክ፥ባህል፥ዕምነት፥ኩራት፥ማንነቱን፥የዜግነት መለያውንና ብሄራዊ እሴቱን ሀገራዊ አንድነቱን ሁሉ ሳይቀር አሚጥጠው ዘርፈውታል። የተተኪውን ትውልድ ዜግነት ሁሉ ሳይቀር ፈልሶ-ተፋልሶና ወድሞ እንዲቀር እያደረጉት ነው። ይሄዳል መሬቱ፥ይጓዛል ሀገሩ፥ ይሸሻል አፈሩ፥እግር አውጥቶ እንደሰው ጀግና የጀግና ልጅ ሄዶ ካልመለሰው የሚባለው የጥቃትና የውርደት እንጉርጉሮ ፥ዛሬ ዋጋ ቢስ እንዲሆን ሊቆጠር የቻለው ፥ የሚተካ ጀግና ትውልድ ሳይቀር ፥ ለጥፋት እየታጻረገ በመሆኑ ነው። የነገዋ ኢትዮጵያ መኖር አለባት ተብሎ መወሰን ካለበት፥የዛሬዋን ኢትዮጵያ ማዳን ብቻ ሳይሆን፥ የነገዋንም ኢትዮጵያ የሚጠብቅ፥ የሚገነባና ነፃነቷንም የሚከላከልላት ትውልድ ዛሬ መወለድ ፥ መፈራትና መዘጋጀት ያስፈልገዋል። የወያኔ ሌቦች እየሰረቁና እየዘረፉ ያሉት የዛሬዋን ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን፥የነገይቱንም ሀገር ህይወትና ሀብት ጭምር እንደሆነ ልብ ተብሎ ሊጤን ይገባል።“የተናቀች ከተማ በአህዮች ትወረራለች” እንደሚባለው ያች የአብዮታውያን ማዕከልና የአናብስት መናሃሪያ የነበረችው አዲስ አበባ ከተማ ዛሬ የወያኔ ሌቦች መጫወቻና መቀለጃ ሆናለች።ጀግኖቿም እንደ አረጀ አንበሳ የዝምብ መቀለጃ ሆነው ቀርተዋል ። እራሱን አዋርዶ ሀገሪቱንም ያስናቀ ደርግ መሆኑ በታሪክ የተመዘገበ መሆኑ ባይካድም ፥ እኛ ግን ዛሬ ትኩረታችን በወደቀ ግንድ፥

ማለትም በደርግ ላይ ሳይሆን፥ ዛሬ ሀገራችንን በሁለንተናዊ አቅጣጫ በመዝረፌ ላይ ባሉት በወያኔዎቹና በተባባሪዎቻቸው ላይ ነው። ምክንያቱም፥ ሌቦቹ የሚሰርቁት ብሄራዊ ሀብት ንብረት ብቻ ሳይሆን ፥ዜጎቿም በሥነ አዕምሮም ረገድ ጭምር ሰለባ እንድትሆን፥ ይሁነኝ ተብሎ የሚደረግ ብሄራዊ ዘመቻ እንደሆነ ማንም ኢትዮጵያዊ የሚስተው አይደለም ። ዛሬ በሀገራችን የሚፈፀመውን መጠነ ሰፊና ዐይን ያወጣ ዝርፊያ ከማንኛውም ጊዜና ሁኔታ የከፋ፥አደገኛና አሳሳቢ ሊያደርገው የቻለው፥ዘራፊዎቹ ልክ እንደ ውጭ ቅኝ ግዛት ወራሪዎች ሁሉ፥ ዝርፊያቸውን የሚያራምዱት፥በግልፅ፥ስርቆታቸውንም የህግ ሽፋን መስጠታቸውና ዘራፊዎቹም እነርሱ ያወጡትን ህግ ተርጓሚዎችና አስፈፃሚዎች በመሆናቸው ነው። ህጉም “ህጋዊ” ቀማኛውና ዳኛውም ፖሊሱና ጠበቃውም በአንድ ትልቅ የሌቦች ኩባንያ ስር ተደራጅተውና ተሰባስበው ልክ እንደ ኢጣሊያ ማፊያ ወይም የወንበዴ ቡድን ድርጊታቸውን ሁሉ ያለፍርሃትና ያለይሉኝታ ያካሂዳሉ ።ይህንንም የዝርፊያ ሂደትና አፈፃፀም አብዛኛው ሕዝብ እያየ እየሰማ ፥ዓይኑንና ጆሮውን እስከ መጠራጠር ደረጃ ለመድረስ መብቃቱ አርቆ ለሚያስብ ዜጋ፥የወያኔዎችን ፥የአይን አውጣነት ችሎታ ሳያስገርመው አይቀርም።

ወያኔዎቹ ፥ ሀገራችንን በሁለንተናዊ መልኩ ለመዝረፍና ይህንንም ዘረፋ የረዥም ጊዜ ዕድሜ እንዲኖረው ለማድረግ እንደ ድልዳል የሚጠቀሙበት ፥ የራሳቸውን ድርጅት ደንብና መዋቅር ወደ ሀገሪቱ ህገ መንግሥት ለውጠው መጫናቸውና የሚያዋርድ የቁማር ጨዋታ መጫወታቸው ነው። ይህን ዘዴ የህግ ማጠየቂያ ለማድረግ በመቻላቸው፥ ከውጭ የሚያገኙትን የዓለም አቀፍና የመንግሥታት ዕርዳታዎች ያለምንም ተጠያቂነትና ኃላፊነት እንደልባቸው ለራሳቸው ጥቅምና አገልግሎት ይጠቀሙበታል።ይህ ድርጊት የሀገሪቱ ብቸኛ አምባገነን ለመሆን ያስቻላቸው ብቻ ሳይሆን ፥ የሀገራችንን ብሄራዊ ልዕልናም ሆነ የነፃነት ክብር ለበላይ ጠባቂዎቻቸውና አሳዳሪዎቻቸው እንዳለ ለማስረከብ ሁሉንም ነገር አመቻችቶላቸዋል። ከእነርሱ በፊት ከነበሩት ሁለት አምባገነን ሥርዓቶች በእጅጉ ከሚለዩአቸው መሠረታዊ ጉዳዮች

መካከል አንዱ፥ የሀገራችንን ሁለንተናዊ ነፃነትና ኅልውና ለባዕዳን አሳልፈው መስጠታቸው ነው:: ግን፥ ሀገር ወዳድነት የሚባል ባኅርይ ስለሌላቸው ይህንን ቢያደርጉ ማንም ኢትዮጵያዊ ሊገረም ከቶ አይችልም:: የፖለቲካ ቁማር አጨዋወት ርካሽ ብልጠታቸውን በሚገባ ሊያስመሰክሩ የቻሉበት ፥ ህገ መንግሥት ብለው በሞጫጨሩት ወረቀት ላይ ያሰፈሯቸው ሁለት አንቀጾች ናቸው::አንቀጽ ሁለትና አንቀጽ ሠላሳ ዘጠኝ መሆናቸው ነው:: ለስርቆታቸውና ሀገሪቱንም ለማጥፋት እንዲመቻቸው እነኝህን ሁለት " የህገ መንግሥት " አንቀጾች አንዱ ከሌላው ጋር ተደጋጋፊና አጠነካካሪ እንዲሆኑ የተቀረጹ ናቸው:: አንቀጽ ሁለት የየክፍላተ ሀገሮች ድምበር በየጊዜው እንዲበወዙና ያለማቋረጥ እንዲለዋወጡ የህግ ማጠየቂያውን እንደ ድልዳል ሲያመቻች፥ አንቀጽ ሠላሳ ዘጠኝ ደግሞ ፥ ጭራሹንም የኢትዮጵያ ዜጎች የየሚኖሩባቸውን ክፍለተ-ሀገር እንደያዙ ወደየሚሄዱበት እንደዲሄዱ"የህግ"ምርኩዝና ማጠየቂያ ሰጥቷቸዋል:: ለዚህ ክስተት እንደ ዓይነተኛ ማስረጃ ሆኖ ሊጠቀስ የሚችለው፥ የወያኔ መሪዎች፥ ከጎንደር፥ ከወሎና ከአፋር በግድ የወሰዷቸው መሬቶችና በሚያስፈልጋቸው ጊዜ፥ ሠላሳ ዘጠኝ አንቀጻቸውን በመጠቀም ትግራይን አስገንጥለው ዓለም አቀፍ ዕውቅናን የመያገኙበት ስትራተጂያዊ ግባቸውን ለማረጋገጥ ነው:: እነኝህ የወያኔን እኩይ ዓላማ ለማስፈጸም ተብለው የተቀረጹ ምግባረ-አሪዮስ አንቀጾች ግን ለአስገንጣይና ለተገንጣይ ቡድኖች ማጠፊያው እንዳይቸግራቸው ያዘጋጀላቸው አንዳችም የመከላከያ መስመር የለም:: የወያኔን መሪዎች በብሔራዊ ክህደትና የዘር ማጥፋት ወንጀል ከመከሰስ ሊከላከሉላቸውም ከቶ አይችሉም::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ ከማነኛውም በፊትና በበለጠም ሁኔታ የሚፈልገው፥ ዘላቂ ሠላምን አግኝቶ ከረሀብና ከቸነፍር ነፃ የሚያደርገውን ሁኔታ ማመቻቸት ነው:: ይህንን ሁኔታ ደግሞ ሌቦች ጭራሽ እንዲመጣ የሚፈልጉት አይደሉም:: የማይፈልጉበትም ሁለት ምክንያቶች አሏቸው:: አንደኛው፥ " የገበያ ግርግር ለሌቦች ይመቻል " እንደሚባለው፤ ግርግር ከሌለ ስርቆትና ዝርፊያ እንደልብ ስለማይገኝ ነው:: ሁለተኛ ምክንያት፥ በኢትዮጵያ ሠላም ሰፍኖ፥ መረጋጋት

ተገኝቶ፥የህግ የበላይነት ነግሦ፥የዜጎች ልዕልና ተረጋግጦ፥መልካም አስተዳደር ተጠያቂነትና ኃላፊነት ከተዘረጋ ፥ በፍትኅ-ርትዕ ላይ የተመሠረተ ዳኝነት የኢትዮጵያን ሕዝብ ሰብዓዊ መብትና ነፃነት ዋስትና ስለሚያረጋግጥ ነው ። ይህ በሚሆንበት ወቅት ደግሞ ሌቦችና ዘራፊዎች፥ ወንጀሎችና ከሃዲዎች ለፍርድ መቅረባቸው የማይቀር ይሆናል። ያ በሚሆንበት ወቅት ፥ ጦርነት ያፈራቻቸው ሌቦች በሠላም ወቅት በፍርድ ይቀጣሉ ። ለዚህም ነው የወያኔ መሪዎች፥በየጊዜው ጦርነትና ብጥብጥ፥ፍጅትና ሁከት የአገዛዛቸው ዓይነተኛ ዘዴ ያደረጉት። ያም ቢሆን፥ " የማታ ማታ ዕውነት ትረታ " እንደሚባለው በመጨረሻ በሀገራችን ሠላም ሲሰፍን ሁሉም እንደ ድርጊቱ እንደ ምግባሩ ፥ የሚፈረድለትና የሚፈረድበት ይሆናል። ምክንያቱም ፥ ምንም ቢዘገይ ፥ ከታሪክ ፍርድ ሊያመልጥ የሚችልና ከህግም በላይ ሊሆን የሚችል ስለማይኖር ነው።